# እኔስ ….. ተናገርኳት!

ከአክሊሉ ሃይሉ

ስምሽን አላስታውሰው፣ ደግሜ አልጠራበት፣
ስምሽ ነው ጠንቀኛው፣ የእድሜ ልክሽ ጠላት።
ደምሽ ተንጠፍጥፎ፣ ይድረቅ ለወዲያኛው፣
እሱ ነው ስሪትሽ፣ የዘርሽ መገኛው።
ማጠንሽም ይንጠፍ፣ ይምከን እንደ በቅሎ፣
እስከመቼ ድረስ፣ ስንቱን ጉድ አብቅሎ።

አንጀትሽ ተፈትቶ፣ ይበተን ከሜዳው፣
ከሆድሽ መሽጎ፣ ዘር እሚያጋምደው።
ልብሽን ሰንጥቀው፣ ይዩብሽ ጉድሽን፣
መውደድ ጥላቻሽን፣ ሐዘን ደስታሽን።
ያየር ከረጢትሽ፣ ትንፋስሽ ይቋረጥ፣
ነፍስ እያቋደሰ፣ ትውልዱን ከሚያስምጥ።

ክንድሽንም አጥፈው፣ ከደረት ይሰሩት፣
ሁሉን እያቀፈ፣…………..
ስንቱን ከሚያዋትት፣ ስንቱን ከሚያሚግት።
እግርሽ ሽባ ይሁን፣………
እርሻ አትሂጅበት ፣ ውሀም አትቅጅበት፣
ቃርሚያ እየሰበሰብሽ፣ ግርድ አታመርችበት።

ስስት እማያውቀው፣ ይታሰር አንጀትሽ፣
ፈትፋችና አጉራሹ፣ ጣትሽ ነው ደመኛሽ።
የናትነት ጓዳሽ፣ ሴትነትሽ ይክዳሽ፣
ሴት በመሆንሽ ነው፣ የሚያንከራትትሽ።
ጆሮችሽ ይንተቡ፣ መስማት ያቅታቸው፣
ውርደትሽን መስማቱ፣ ላይ እንባ ቀለብ ነው።

አይንሽን ሾርበው፣ ይጋርዱት በሸማ፣
ምን ያደርግለታል፣ መብቱን ለተቀማ።
መቀነትሽን ፈትተው፣ ያጥልቁልሽ ሱሪ፣
አሳብ ነው ልጅ መውለድ፣ አንች ድሃ! አዳሪ።
እኔም እናቴ አልበል፣ አንችም ልጄ አትበይኝ፣
ወፍዘራሽ ማንዘራሽ፣ የቲም ልጅ ከሆንኩኝ።

ቀብሬን ይማሱና፣ መርዶዬን ይንገሩሽ፣
አንችም አታልቅሽ፣ እኔም ባይኔ አልይሽ።
የኔን ነገር ለሷ፣ ተዋት አትንገሯት፣
ወለደችኝ እንጅ፣ እኔ መች ወለድኳት።
የልቤ እንባ ፈሶ፣ አንጀቴን አራሰው፣
መውለድ ምን ያደርጋል፣ ልጅ እዬከዳው ሰው፣

መውለድ ክብር ሁኖ ፣ ወግ ማረግ ካልታዬ
በካር ምን መቅኖ አላት፣………
ቤቷ ከደኸዬ፣ ሽሏ ከጎፈዬ፣ ክብሯ  ከጠኸዬ !!!

ከፍራንክፈርት - (ጃንዋሪ — 2012)